በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 5!!!

## ፕሮቴስታንቲዝም - 2

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

የካቲት ፲፫ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## ዋነኞቹ የፕሮቴስታንት ‹‹አብያተ ክርስቲያናት››

1. ሉተራን 2. ባፕቲስቶች 3. ሜቶዲስቶች

## የሉተራን አጀማመር

- ሉተራኒዝም የፕሮቴስታንት ትልቁ ቅርንጫፍ ሲሆን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጀርመናዊው ሉተር የተጀመረው ትምህርት መታወቂያ ምልክታችን ነው ይላሉ፡፡
- የተሐድሶ እንቅስቃሴው ከፈጠራቸው የፕሮቴስታንት ክፍሎች በተለየ መልኩ ከተሐድሶ በፊት የነበሩ አንዳንድ ምስጢራትንና የአምልኮ ሥርዓቶችን ለመጠበቅ ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡
- መለኮታዊ ጸጋንና ዘላለማዊ ሕይወትን አስመልክቶ በሉተራኖች ዘንድ ያለው አስተምህሮ ከተሐድሶ ክፍሎች በጥቂቱ ይለያል፡፡
- በአሁኑ ወቅት በዓለም 70 ሚሊዮን ያህል የሉተራን ተከታዮች ሲኖሩ 400 ሚሊዮን የሚሆኑት የፕሮቴስታንት ‹‹ክርስቲያኖች›› ራሳቸውን ከሉተራን ተሐድሶ አጀማመር ጋር ያገናኙታል፡፡
- የሉተራን ወንጌላውያን ‹‹አብያተ ክርስቲያናት›› በሰሜን አውሮፓ የመንግሥት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ነበሩም፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## የሉተራን እምነት

- የሕጻናትን ጥምቀት ይቀበላሉ፡፡ ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን የሚቀበሉአቸው ምስጢራት ናቸው፡፡
- ድኅነት የእግዚአብሔር ብቻ የጸጋ ሥራ ነው ይላሉ፡፡
- አንዳንድ ሉተራኖች ‹‹ቅዱስ ቁርባን›› የሚለውን ቃል አይቀበሉትም፡፡
- በሉተራን እምነት - መዳን የእግዚአብሔር የጸጋ ሥራ ነው፡፡
- በነርሱ አገላለጥ መዳን ከእግዚአብሔር ሲሆን ሰው ለመዳኑ የሚገባውንና የሚጠበቅበትን አለመፈጸሙ መዳኑን እንዳይፈጸም እንደሚያደርገው አያምኑም፡፡ ይህም የወደቀው ሰው ለመንፈሳዊ ነገር ያለውን ነጻ ፈቃድ ይክዳሉ፡፡
- ሉተራኖች ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ዕዳው ተከፍሎለታል፣ በኢየሱስ ክርስቶስም ጽድቅ ያለ ምንም ውጣ ውረድ ይጸድቃል፣ እንዲሁም ሰው እምነቱ በክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሆነ ነው በማለት የሥራን (የመንፈሳዊ ምግባራትን) - የንስሐንም አስፈላጊነት ከንቱ ያደርጉታል፡፡
- ይህም ሆኖ ቅዱስ ቁርባንን አምላካዊ ነው ብለው ቢቀበሉትም ሁለቱንም በአንድ ላይ አድርገው ያቀብሉታል ይቀበሉታል፡፡
- አንዳንዶቹም ለተጠመቁት ሁሉ ያለ ልዩነት የሚያቀብሉት ሲሆኑ አፈጻጸማቸውም መጋረጃውን ሙሉ ለሙሉ ከፍተው ምስጢሩንም በመግለጥ ይፈጽሙታል፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## *የባፕቲስቶች እምነት*

- ባፕቲስቶች በዓለም በሚገኙ የፕሮቴስታንቶች ቁጥር ሦስተኛውን ደረጃ የሚይዙ ናቸው፡፡
- እነዚህም በተወሰነ መጠን በሉተርና በዝዊንግል ተቀባይነት አጥቶ የነበረው አክራሪነት የተቀላቀለበት የፕሮቴስታንቶች የተሐድሶ እንቅስቃሴ ነው፡፡
- ባፕቲስቶች ‹‹ሁለተኛ የተጠመቁ›› የሚል ቅጽል ስም ነበራቸው፡፡ ይህም ስም የተሰጣቸው በየኤስኤ በተጀመረው እንቅስቃሴአቸው ከሕጻናት ይልቅ የተጠመቁ አዋቂዎችን ዳግመኛ አስገድደው ያጠምቁ ስለነበር ነው፡፡
- በዓለም ላይ የባፕቲስቶች ቁጥር ከ110 ሚሊዮን በላይ ሲሆን 170 ሺህ ያህል የአምልኮት መፈጸሚያ ማዕከላት አሉአቸው፡፡
- ባፕቲስቶች በዓለም ላይ በቁጥራቸው ከፍተኛ እንደሆኑ የሚታወቁ የፕሮቴስታንት ቡድኖች ሲሆኑ በዩኤስ አሜሪካ 22 ሚሊዮን የሚጠጉ ተከታዮች አሉአቸው፡፡
- ሌላው በቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ባፕቲስቶች በእስያ፣ በአፍሪካ እና በላቲን አሜሪካ የሚገኙ ሲሆን ይልቁንም በሕንድ 2.4 ሚሊዮን በናይጄሪያ 2.5 ሚሊዮን፣ በዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ ኦፍ ኮንጎ 1.9 ሚሊዮን እና በብራዚል 1.7 ሚሊዮን ያህል ተከታዮች ይገኛሉ፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## *የባፕቲስቶች እምነት*

- በ1990ዎቹ በዩኤስ አሜሪካ በተደረገ ቆጠራ ከአምስቱ አንዱ ‹‹ክርስቲያን›› የባፒቲስት ተከታይ ነኝ እንደሚል የተጠቆመ ሲሆን ባፕቲስቶች በዩኤስ አሜሪካ ከ50 በላይ በሆኑ የተለያዩ ቡድኖች ይወከላሉ፡፡
- 92 ፐርሰንት የሚሆኑትም ባፕቲስቶች በደቡባዊ ባፕቲስት ኮንቬንሽን (SBC)፣ በናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን - በዩኤስ አሜሪካ ኢንኮርፖሬትድ (NBC) ፣ በናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን ኦፍ ዩኤስ አሜሪካ ኢንኮርፖሬትድ (NBCA) ፣ አሜሪካን ባፕቲስት ቸርችስ በዩኤስ አሜሪካና (ABC) ባፕቲስት ባይብል ፌሎው ሺፕ ኢንተርናሽናል (BBFI) ስር የታቀፉ ናቸው፡፡
- ባፕቲስቶች በእነርሱ ከሚፈጸመው ጥምቀት ውጪ አሰቀድሞ በማንኛውም መልኩ የተፈጸመ ጥምቀት ተቀባይነት የለውም ይላሉ፡፡
- ሰው የራሱን ውሳኔ መስጠት እስከሚችልበት ዕድሜ ድረስ መጠመቅ የለበትም የሕጻናትም ጥምቀት ተቀባይነት የለውም ይላሉ፡፡
- ጥምቀትንም ምልክት ነው እንጂ ምስጢር አይደለም ይሉታል፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## የባፕቲስቶች እምነት

- እንቅስቃሴአቸው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተጀምሮ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ቁጥራቸው እየጨመረ መጣ፡፡ ቅርንጫፎቻቸው በትምህርታቸውም ቢለያዩም የሕጻናትን ጥምቀት በተመለከተ ባላቸው ትምህርት ግን አንድ ናቸው፡፡ *ማቴ 19፡14፣ ዮሐ 3፡5፣ ሉቃ 2፡22-24፣ የሐ.ሥራ 16፡15፣ ዘሌዋ 12፡1-8* ግን ይህን አያስተምሩም፡፡
- ባፕቲስቶች የ‹‹ሃይማኖት›› መሪ የሌላቸው ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስን በነጻነት አንብበን በገባን መልክ እየተረጎምን መመራት አለብን ባዮች ናቸው፡፡ ሮጀር ዊሊያምስ በ1635 እ.አ.አ. በአሜሪካን አገር በምትገኝ ደሴት የባፕቲስቶችን ማኅበር አቋቁሟል፡፡
- ባፕቲስቶች በመጨረሻ ከዶግማ፣ ቀኖና፣ … የጸዳን ነን… ፈቃደኛ የሆኑ አማኞችን በመጠቀም ለሽማግሌዎችና ወላጅ ለሌላቸው መኖሪያ፣ የሕክምናና የትምህርት እርዳታ እንሰጣለን በማለት የጥቁር አሜሪካውያንን ልብ ለመማረክ ችለው ነበር፡፡ ይህም በእንግሊዝ፣ በጀርመን በቻይና፣ በጃፓን፣ በሕንድ፣ በፖላንድ፣ በሩሲያ፣… ለመስፋፋት ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡
- ባፕቲስቶች ሥላሴን፣ የሲያልንና የዲያቢሎስንም መኖር (ትምህርት) አያምኑም፡፡ እምነት ብቻውንም በቂ ነው በማለትም የሥራን አስፈላጊነት ይክዳሉ፡፡ *ያዕ 2፡14-19፡፡*

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## የሜቶዲስቶች እምነት

- በ1784 እ.አ.አ. ከእንግሊዝ ቸርች ተገንጥለው በአሜሪካ ሜቶዲስት ቸርች ተብለው ተቋቋሙ።
- የተጀመረውም በአንግሊካኑ ቄስ በጆን ዌስሌይና በጆርጅ ዘዋይት ትምህርት ነው።
- የብልሃት መንገድ (Rule of Method) የሚል መጽሐፍ ጽፈው ስለነበር በዚህ የተነሳ ተከታዮቻቸው ሜቶዲስቶች ተብለዋል። በውስጣቸውም ብዙ ክፍፍሎች አሉአቸው።
- ይህም የሜቶዲስቶች እንቅስቃሴ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በታላቋ ብሪታኒያ በተለያዩ የሚሽነሪ እንቅስቃሴዎች ከተጀመረ በኋላ በመላዋ ብሪታኒያ፣ በዩኤስ አሜሪካና ከዚያ ርቀው በሚገኙ ሌሎች አገሮችም ተስፋፍቷል።
- በመጀመሪያ የ‹‹ተሰበኩት›› ሠራተኞች፣ ገበሬዎችና ባሮች ነበሩ።
- ብዙዎቹ ሜቶዲስቶች አርመናውያንና ካልቪኒስቶች ነበሩ። በ2006 በተደረገ ቆጠራ በመላው ዓለም የሚገኘው ቁጥራቸው 75 ሚሊዮን እንደሚደርስ ጠቅሰዋል።
- ሜቶዲስቶች በሥላሴ፣ በጉባኤ ኒቂያ፣ በምስጢረ ጥምቀትና ቁርባን፣ በትውፊት ለማመን ቢሞክሩም በሌሎቹ ምስጢራት ግን አያምኑም።

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## *ጴንጤዎች (Pentecostalism)*

- በአሜሪካ ቶፔካ በተባለው የካንሳስ ግዛት በ1901 እ.አ.አ. ቻርለስ ፓርሃም በተባለው ሜቶዲስት የተመሠረተ መጤ እምነት ነው።
- ጰንጤዎች ሁለት ዓይነት ናቸው። ሁለቱም የየራሳቸው ክፍፍሎች አሉአቸው። ሁሉም ግን በልሳን መናገርና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ በሚለው ትምህርታቸው ይመሳሰላሉ። በተቀረው ሐሳባቸው ግን የፕሮቴስታንት ዘርፍ ናቸው።
- ሁለቱ የጰየንጤ ዓይነቶች ዩኒታሪያኒዝምና ተሪኒታሪያን ይባላሉ።

## ዩኒታሪያኒዝም (Unitarianism)

- በሥላሴ እናምናለን ብለው መልሰው ክርስቶስን ከአብና ከመንፈስቅዱስ አሳንሰው የሚመለከቱ ናቸው።
- በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ የተጠመቁ ዳግመኛ በኢየሱስ ስም መጠመቅ ይኖርባቸዋል፤ ካልተጠመቁም አይድኑም በማለት ፀረ-ሥላሴ አቋማቸውን ይገልጣሉ።
- አብ ወልድ መንፈስቅዱስ የማዕረግ ስሞች እንጂ የአካላት ስሞች አይደሉም፣ አብ ወልድ መንፈስቅዱስም ኢየሱስ ብቻ ነው ይላሉ። የዩኒታሪያኒዝም ሌላኛው ስማቸው ዋን ነስ ቸርች (Oneness Church) ይባላል።
- በኢትዮጵያ ያለው ቅርንጫፋቸው የኢትዮጵያ ሐዋርያት ቤ/ክ ተብሎ የሚጠራው ነው።

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## *ጴንጤዎች (Pentecostalism)*

## ትሪኒታሪያን (Trinitarian)

- ክርስቶስ በማኅፀነ ዮርዳኖስ ጸጋ መንፈስቅዱስን ባይሞላ ኖሮ ሰይጣንን በገዳም (በምድረ በዳ) ሳለ ሊያሸንፈውና ተአምራትንም ሊሠራ ባልቻለ ነበር በማለት በአማላጅነት መድበውት ጸጋ ሰጪ ሳይሆን ተቀባይ ነው በማለት የክህደት ትምህርታቸውን ያሠራጫሉ።
- እነዚህ ብዙ ቅርንጫፎች አሉአቸው። ከቅርንጫፎቻቸውም መካከል በ1906 እ.አ.አ. የተመሠረተው የሙሉ ወንጌል አማኞቻ (Full Gospel) ተብሎ የተሰየመው አንዱ ነው።
- እነዚህ በጥቂቱ ሃያ ስድስት ቅርንጫፎች ያሉአቸው ሲሆን ጥቂቶቹም አሴምብሊስ ኦፍ ጎድ (Assemblies of God)፣ ቸርች ኦፍ ጎድ ኢን ክራይስት (Church of God in Christ) ፣ ዩናይትድ ፔንቴኮስታል ቸርች (United Pentecostal Church) ተብለው ተሰይመዋል።
- በኢትዮጵያ እነ ሙሉ ወንጌል፣ መሠረተ ክርስቶስና ቤቴል የመሳሰሉት የዚህ ቅርንጫፎች ናቸው።
- … ከዚህ የተቀረውን ‹‹እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?›› በሚል ርዕስ የተሰጠውን አሥር ተከታታይ ክፍሎች ያሉትን ትምህርት ያንብቡ።

# ፕሮቴስታንቲዝም - 2

## ሞርሞኒዝም (Mormonism)

- የኋለኛው ዘመን(ቀን) ቅዱሳን በመባል የሚታወቁ ሲሆኑ በ1825 እ.አ.አ. በአሜሪካ ተፈጠሩ፡፡ አሁን ወደ 2.5 ሚሊዮን የሚጠጉ ተከታዮች አሉአቸው፡፡ መሥራቹም ዮሴፍ ስሚዝ ይባላል፡፡
- ዮሴፍ ስሚዝ ‹‹ቡክ ኦፍ ሞርሞንስ›› የሚል መጽሐፍ ከጻፈ በኋላ ተከታዮቹ መጽሐፉን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ቆጥረውታል፡፡ በመጽሐፉም 600 ከክ.ል.በፊት ወደ አሜሪካ የተሰደዱ አይሁድ እንደነበሩና እነርሱም በጫካው ይኖሩ ነበሩ ለተባሉት ሕንዶች መገኛ ናቸው ተብሎ ተገልጧል፡፡
- እነዚህም በ‹‹ኢየሱስ›› እንደተበኙና ጥበበኞች፣ ለሕንጻ ሥራም መነሻ የሆኑ ከተሞችም እንዲመሠረቱ ምክንያት የሆኑ ናቸው በሚል መጽሐፉ አጉልቶ ይናርላቸዋል፡፡
- ‹‹ኢየሱስ›› በጎበኛቸውም ጊዜ ያስተማረው ትምህርት በነቢያችን በሞርሞን አማካይነት በወርቅ ጽላት ተጽፏል ይላሉ፡፡
- ሞርሞኖች ቡና ወይም ትምባሆ አይጠቀሙም፣ አልኮልም አይጠጡም፡፡ ብዙ ማግባት ግን አይከለከሉም፡፡
- ሞርሞኖች የስሚዝ መጽሐፍ ከመጽሐፍ እኩል ነው፣ እርሱም እንደ ነቢዩ ሙሴ ቅዱስ ነው እንዲያውም ‹‹ኢየሱስን›› ይተካከለዋል ይላሉ፡፡
- *‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ፡፡›› ኤር 6፡16፡፡*
- ***ታዲያ እኛ የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት በዓለም ሁሉ እንዲስፋፋ ምን እያደረግን ነው?_‹***
- *‹›ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና፡፡›› ሮሜ 10፡10፡፡*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org